# እንኳን ለ2014 ዓ.ም በሰላም እና በጤና አደረሳችሁ!!!

የ2013 በጀት ዓመት የፍርድ ቤቱን የለውጥ ስራዎች የሚያግዙ በርካታ መደላድሎች የተሰሩበት ጊዜ ነበር፡፡ የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ አዋጆችን ጨምሮ በርካታ መመሪያዎች እና የአሰራር ስርዓቶች የተዘረጉበት ዓመት ነበር፡፡

ከእነዚህም የለውጥ መደላድሎች በተጨማሪ በመደበኛ የዳኝነት ስራችን በማጥራት ምጣኔም ሆነ የመዝገብ ክምችትን በመቀነስ ይበል የሚያሰኝ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ የተገኙ መልካም ውጤቶችም የፍርድ ቤቱ ማህበረሰብ የጋራ ጥረት ውጤት በመሆናቸዉ ሁላችንንም የሚያኮሩ ናቸው፡፡ በተቃራኒው በ2013 እና ከዚህም በፊት በነበሩት ዓመታት የነበሩ አሁንም ድረስ ያልቀረፍናቸው ችግሮች ወደ አዲስ ዓመት ይዘናቸው እንዳንሻገር በትኩረት መስራት ያስፈልጋል፡፡

በተለይም በፍርድ ቤታችን የሚስተዋሉ የስነ-ምግባር ችግሮችን ያለ ርህራሄ ማስወገድ ወይም መታገል ያስፈልጋል፡፡ በዳኞችም ይሁን በድጋፍ ሰጪ ሠራተኞቻችን አካባቢ በሚስተዋሉ እና እያደጉ የመጡ የስነ-ምግባር ችግሮች በጊዜ ካልተቀረፉ ተቋማችን ፍትህ/ዳኝነት የመስጠት የሞራል ልዕልና ሊኖረው አይችልም፡፡ በእርግጥ እነዚህ የስነ-ምግባር ግድፈቶች የሚታይባቸዉ ዳኞች እና ሠራተኞች በቁጥር ውስን ቢሆኑም አብዛኛው የፍርድ ቤቱ ማህበረሰብ ነገሮችን በዝምታ የሚያልፍ እና የማይታገል፣ አንዱ ሌላውን የማያርም በመሆኑ የጥቂቶቹ ችግር የተቋሙ እና የበርካታ ንፁህን ዳኞች እና ሠራተኞችን ስም ማጠልሸት ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በ2014 ዓ.ም የፍርድ ቤቱ አመራርም ሆነ ማህበረሰብ የላቀ ስነ-ምግባር በተቋማችን ለማስፈን የሚደረገውን ጥረት ከልብ ማገዝ ይጠይቃል፡፡

በሌላ በኩል የዳኝነት ስራ መጓተትን ለማስቀረት ታስቦ የፀደቀው የፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍትሃብሄር ጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያ በጥብቅ መተግበር የ2014 ዓ.ም አብይ ጉዳያችን ይሆናል፡፡

በየዓመቱ የሚተላለፉ መዝገቦች መብዛት አንድን ጉዳይ እልባት ለመስጠት የሚወስደውን ጊዜ የሚጨምር በመሆኑ ይህም የዜጎችን ፍትህ በጊዜው የማግኘት መብትን የሚጥስ በመሆኑ መላው የፍርድ ቤቱ ማህበረሰብ ለመመሪያው ተግባራዊነት በቁርጠኝነት መስራት ይኖርብናል፡፡

የፍርድ ቤቱ አመራር ግብ መመሪያውን በማፅደቅ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን መመሪያው እንዲተገበር ማድረግ በመሆኑ ለተግባራዊነቱ በቁርጠኝነት የምንሠራ ስለሆነ ሁሉም የፍርድ ቤቱ ማህበረሰብ በተለይም ዳኞች ይህን መመሪያ በየችሎቶቻቸው በጥብቅ እንዲተገበሩ አደራ እያልኩኝ 2014 ዓ.ም መልካም የስራ ዘመን እንዲሆን እመኛለሁ፡፡